# በአባይ ስሞች ውስጥ ምን አለ? የተቀማነው ስማችንንም ነው?[1]

ሙሉሰው አስራቴ[2]

**አኅጽሮተ ጥናት**

ይህ ጽሑፍ ከጥንት እስከዛሬ ለአባይ ወንዝ መጠሪያ ሆነው ያገለገሉ ስሞችን በመሰብሰብ የትመጣቸውንና ፍቻቸውን ከወንዙ ጋር አብረው ከኖሩ ህዝቦች ቋንቋ፣ ባህል እና የስም አሰጣጥ ልማድ አንጻር ይመረምራል፡፡ አባይ በጥንት ጊዜ ሃፒ/ሃቢ፣ አር/ውር/ ሂሖር፣ ፒያሮ/ፊያሮ/ ኢትርው የሚባሉ ስሞች ነበሩት፣ አሁን ደግሞ ግዮን፣ አባይና ናይል በሚባሉ ስሞች የሚታወቅ ነው፡፡ የእነዚህ ስሞች የትመጣና ፍች ግን አንዴ አውሮፓዊ፣ አንዴ ደግሞ ግብጻዊ ብቻ ሲደረግ ኖሯል፡፡ ይህ ጥናት የአባይን የጥንትም ይሁን የአሁን ዘመን ስሞች የትመጣና ፍች፣ ታሪክን፣ የስም አወጣጥና ለውጥ ልማድን መሠረት በማድረግ፣ ከዛሬዎቹ ግብጻውያንና አውሮፓውያን ይልቅ፣ ከወንዙ ጋር አብረው ከኖርነው ኢትዮጲያውን ጋር የተቆራኘ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የወንዙ መጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ስሞች በሀገር ደረጃ አዎንታዊና አሉታዊ ስሜቶችን በተደራቢነት እንደሚገልፁም ለማሳየት ይሞክራል፡፡

**ቁልፍ ቃላት**፡- ስም፣ ስመ-ተጸውኦ፣ አባይ፣ ናይል፣ ግዮን፣ አር/አውር/ ሂሖር፣ ፒያሮ/ ፊያሮ/ኢትርው

## 1. መግቢያ

አባይ የርዝመቱን ያህል ብዙ ስመ-ተጸውኦዎች ያሉት ወንዝ ነው፡፡ ይህ ጥናት የአባይን ስሞች ከሰያሚዎች ታሪክ፣ ባህልና የስም አወጣጥ ሥርዓት አንጻር ይመረምራል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የአባይ መጠሪያ ሆነው እያገለገሉ ያሉ ስሞች በወንዙ ዙሪያ ባሉ የሀገራችን ህዝቦች ምን አይነት ተደራቢ ፍችዎች (ስሜትና ሐሳብ) እንዳዘሉ ይፈትሻል፡፡

የጥናቱ መረጃዎች ከመስክ እና ከሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ የመስክ መረጃዎች በ2008 እና 2009 ከአማራ ክልል የተለያዩ ቦታዎች (ደጀን፣ ባሶሊበን፣ ሰከላ፣ እነማይና ሸበል በረንታና መራዊ ወረዳዎች እንዲሁም ከባህር ዳርና ደብረ ማርቆስ ከተሞች) በምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ለጥናቱ የተፈተሹ ሰነዶችም የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጥናቶችና መዛግብት ናቸው፡፡

ጥናቱ በስድስት ክፍል የቀረበ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ይህ መግቢያ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል የስመ-ተጸውኦ ፍች በስም ጥናት ምን እንደሚመስል ትውረታዊ ጉዳዮች የተዳሰሱበት ነው፡፡ የአባይ ስሞች የትመጣና ፍች በሦስተኛው ክፍል ይመረመራሉ፡፡ በአራተኛው ክፍል በአባይ ስሞች ላይ ያለው እሰጥ አገባ ይዳሰሳል ይመረመራል፡፡ አምስተኛው ክፍል ደግሞ በአሁኑ ወቅት

---

[1] ይህ የጥናት በዶክተር መርሻ አለኸኝ መሪነት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጋፍ *የናይል ጉዳይ (The Nile Quest)* በተባለ የምርምር ፕሮጀክት ሥር የተደረገ ነው፡፡ ለዶክተር መርሻ አለኸኝና ለአዲስ አበባ ዩኒርሲቲ መስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

[2] mulusew.asratie@aau.edu.et

ከአባይ ስሞች ጋር ምን ምን ተደራቢ ስሜቶች እንዳሉ ይዳስሳል፡፡ ስድስተኛው ክፍል መደምደሚያ ነው፡፡

## 2. የስመ-ተጸውኦ ፍች

ስም የሚለው ቃል ሁለት የተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦችን ይወክላል፡፡ አንደኛው አጠቃላይ የሆነ የሰዎች፣ የነገሮች፣ የቁሳቁስ መጠሪያ (Noun) ነው፡፡ ሰው፣ በግ፣ ትምህርት፣ መኪና ወዘተ. የመሳሰሉት ቃላት ስም ተብለው ይጠቀሳሉ፡፡ እንዲህ አይነት ስሞች ተመሳሳይ ባህርይን፣ ግብርን ለሚጋሩ ነገሮች የጋራ መጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለአንድ ንጥል ቁስ፣ሰው ወይም ነገር ብቻ መጠሪያነት የሚሰጥ መለያ (Name) ነው፡፡ በአማርኛ እንዲህ አይነት ስሞችን ከአጠቃላይ ስሞች ለመለየት ስንፈልግ ስመ-ተጸውኦ እንላቸዋለን፡፡ ስመ-ተጸውኦ ከሌሎች ስሞች በተለየ ለአንድ ነጠላ ነገር መጠሪያነት ብቻ ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ ወዘተ. የሚሉት ስመ-ተጸውኦዎች ለአንድ ነጠላ ቦታ፣ ተቋም ወይም ግለሰብ መጠሪያነት ብቻ ያገለግላሉ፡፡

በስም ጥናት (Onomatopics) የአጠቃላይ ስም (Noun) እና የስመ-ተጸውኦ (Name) ፍች በተመሳሳይ መልክ አይታይም (Zabeeh 1968፣ Nyström 2016)፡፡ የአጠቃላይ ስሞች ፍች፣ ስሞቹ የሚወክሏቸው ነገሮች፣ ሰዎች፣ ፍጥረታት የጋራ የሆኑ ባህርያትን በመግለጽ ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ *መኪና* ማለት ምን ማለት ነው ተብሎ ሲጠየቅ እንደ ፍች የሚወሰደው መኪኖች ሁሉ የሚጋሯቸውን የጋራ ባህርያት መሠረት በማድረግ *በጎማ ላይ እየተሽከረከረ የሚሄድ ባለሞተር መጓጓዣ* ልንል እንችላለን፤ *መኪና* የተባለ ሁሉ በጎማ የመሽከርከር፣ ባለሞተር የመሆን እና ለመጓጓዣ የማገልገል ባህርያትን ስለሚጋራ፡፡ የስመ-ተጸውኦ ፍችን በሚመለከት ግን የስም ጥናት ምሁራን ሁለት ጽንፍ ያለው ሙግት ያካሂዳሉ፡፡ የአንደኛው ጽንፍ አቀንቃኞች ስመ-ተጸውኦ ተጠሪ (Reference) እንጂ ፍች የለውም ባይ ናቸው (Saul Kripke 1972 እና Keith Donnellan Keith Donnellan 1972፣1974 በNyström 2016:39 እንደተጠቀሱት) ፡፡ እንደዚህ ጽንፍ አራማጆች አባባል ስመተጸውኦ ተጠሪውን ከመጠቆም የዘለለ ሚና የለውም፡፡ ለምሳሌ *ጎጃም* ለሚለው ቃል *በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ እንዲህ እንዲህ ያለ አካባቢ* የሚል ብያኔ ቢሰጥ፤ ይህ ብያኔ *ጎጃምን* ከሌሎች ቦታዎች ነጥሎ ለማመልከት የሚያገለግል እንጂ ከዚህ በላይ እንዳየነውና *መኪና* ለሚለው ቃል እንደሰጠነው ብያኔ በ*ጎጃምነት ውስጥ* ሊወከሉ የሚገባቸውን ነገሮች የጋራ ባህርይ የሚገልጽ አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር መግለጫው *ጎጃም* በሚለው ቃል የተጠራውን ተጠሪ ነጥሎ ይጠቁማል እንጂ የቃሉን ፍች አያመለክትም፡፡ ለዚህ ማስረጃው፣ *ጎጃም* የሚለው ቃል የሰው መጠሪያ ሆኖም መገኘቱ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የለወጥነው ተጠሪውን እንጂ የቃሉን ፍች አይደለም፡፡ ከላይ ለጎጃም የተሰጠው የቦታ ስም የቃሉ ፍች አካል ቢሆን ኖሮ በዚህ መልክ ቃሉን ለሰው መጠሪያ ማድረግ አይቻልም ነበር፡፡ ስለዚህም ስመ-ተጸውኦ ተጠሪ/ተጠቃሽ እንጂ ፍች የለውም ይላሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ክርክር ግን ተቀባይነቱ እየቀነሰ ሄዷል፡፡ ለተቀባይነቱ መቀነስ የሚጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች ናቸው፡፡ አንደኛው ስመ-ተጸውኦ ተጠሪውን ለመጠቆም ብቻ የቆመ ቢሆን ኖሮ ህልውናው ከተጠሪው ህልውና ጋር የተያያዘ ይሆን ነበር፡፡ ሆኖም ተጠሪው ሲጠፋ/ሲሞት ስመ-ተጸውኦው አብሮ ስለማይጠፋ/ስለማይሞት ስሙ በራሱ ከተጠቋሚው ውጭ ህልውና ያለው መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከዚህ በታች

እንደምናየው ስመ-ተጸውኦ ሲጠራ/ሲታወስ አብሮ የሚከሰት ተደራቢ ሐሳብ/ስሜት መኖሩ ነው፡፡ ለምሳሌ ሒትለር የሚለው ስም ከተጠሪው ግለሰብ በተጨማሪ የሚያስታውሰው ተደራቢ ሐሳብ/ስሜት አለ (Zabeeh, 1968: 48)፡፡ ጨካኝነትን ይገልጻል፡፡ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ስመተጸውኦ ፍች የለውም የሚለውን ጽንፍ ጥያቄ ውስጥ ከተውታል፡፡

ሁለተኛው ጽንፍ ስመ-ተጸውኦም እንደሌሎች ስሞች ሁሉ ፍች አለው ብለው የሚከራከሩ ምሁራን ያሉበት ነው (Otto Jespersen (1924) እና Jerzy Kuryłowicz (1980) በNyström 2016: 40 እንደተጠቀሱት) ፡፡ የዚህ ጽንፍ አቀንቃኞች ወደ ስመ-ተጸውኦ ፍች ከማምራታቸው በፊት *ፍች* ዘርፈ ብዙ መሆኑን በማሳየት ይጀምራሉ (Nyström 2016፡ 40-52)፡፡ በዚህም መሠረት ፍችን እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ዘርፎች ይኖሩተል፡፡ እማሬያዊ ፍች በቃላት የሚወከል ቀጥተኛ የፅንሰ ሐሳብ ይዘት ነው፡፡ ለምሳሌ *እናት* ማለት *ሴት ወላጅ* ማለት ነው፡፡ «<u>እናቴ</u> ደግ ናት፣ የካሣ <u>እናት</u> መጡ፡፡» ስንል ቃሉን በእማሬያዊው ፍች ነው የተጠቀምነው፡፡ በተጨማሪም *እናት* የሚለው ቃል *አዛኝ፣ ሩህሩህ* የሚል ፍች ይኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት እኮ <u>እናት</u> ነው ብንል፣ ለሰው አዛኝ፣ ሩህሩህ፣ ደግ ነው ማለታችን ነው፡፡ ይህ ፍች የቃሉ ፍካሬያዊ ፍች ይባላል፡፡ ፍች በዚህ መልክ ከታየ ስመ-ተጸውኦ ተጠሪ (reference) ብቻ ሳይሆን ፍችም ይኖረዋል፣ ብለው ይከራከራሉ፡፡ ከላይ የጠቀስነው የሒትለርን ምሳሌ ልብ ይሏል፡፡ ስለዚህም የተጸውኦ ስሞች ፍች ሊሸከሙ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡

በተጨማሪም ስለስመ-ተጸውኦ ፍች ሲታሰብ በስም ፍችና በቃላተ ስም (name lemmas) ፍች መካከል ያለውን ልዩነትም መለየት እንደሚገባ ይመክራሉ (Van Langendonck እና Van de Velde 2016፡ 19-21)፡፡ *ቃላተ-ስም* ማለት ለስመ-ተጸውኦነት የሚያገለግሉ ቃላት ናቸው፡፡ ሊዛ፣ ቦሪስ፣ ለንደን፣ ፓሪስ፣ ካሊፎርኒያ፣ አዲስ አበባ የሚሉት ቃላት ቃላተ-ሰሞች ናቸው፡፡ ከ*አዲስ አበባ* በስተቀር ግን ሌሎች ቃላት ብቸኛ ተግባራቸው ለሰው ወይም ለቦታ ስምነት ማገልገል ነው፡፡ ስለዚህም ቃላቱ ነባር ቃላተ-ስም (Proprial Lemmas) ይባላሉ፡፡ እነዚህ ቃላት የቦታዎች/የግለሰቦች ስም ከመሆን ያለፈ ሌላ ፍች የላቸውም፡፡ በመዝገበ ቃላት ውስጥም የተሰጣቸው ብያኔ እንዲህ ያለ ግለሰብ፣ ቦታ ወዘተ. ተብሎ፤ አልያም «የቦታ/የሰው ስም» ተብሎ ነው፡፡ በእንግሊዝኛ መዝገበቃላት እነዚህን ስሞች አስገብተን ብንፈለግ ይህን ሀቅ በቀላሉ ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ በምዕራቡ ዓለም በአብዛኛው የሰዎችም ሆነ፤ የቦታዎች ስም የሚሰጠው በዚህ መልክ ለስመ-ተጸውኦነት ከማገልገል ውጭ ሌላ ሚና በሌላቸው ነባር ስሙ-ቃላት (Proprail Lemmas) ነው፡

*አዲስ አበባ* የሚለው ስም ግን ከነዚህ ይለያል፡፡ ስሙ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ መጠሪያ ከመሆኑም በላይ የየራሳቸው ፍች ካላቸው ሁለት የአማርኛ ቃላት የተፈጠረ ነው፤ *አዲስ* እና *አበባ* የሚሉ ቃላት፡፡ በአንድነት ሲመጡም እንዲሁ *አዲስ አበባ- በቅርብ የፈካ እንቡጥ፣ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ጽጌ* የሚል ፍች አላቸው፡፡ ይህ ፍች የቃላተ-ስሙ ፍች ነው፡፡ አዲስ አበባን ማወቅና *አዲስ* እና *አበባ* የሚሉትን ቃላት ፍች ማወቅ የተለያዩ ናቸው፡፡ በርግጥ አዲስ አበባ ይህን ፍች በያዙ ቃላት የተሰየመችበት በምክንያት አለ፤ ቃላቱም ስለ አዲስ አበባ ምንነት የሚገልጹት ፍች/ሐሳብ አለ፡፡ ሆኖም አዲስ አበባን እንደከተማነቷ ለማወቅ *አዲስ አበባ* የሚሉትን ቃላት ፍች ከማወቅ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡

የአፍሮ እስያዊ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ህዝቦች በአብዛኛው ስመ-ተጸውኦ የሚሰጠው ፍች ባላቸው ቃላት ነው፡፡ እንደ van Langendonck and van de Velde (2016: 20) አባባል እንዲህ አይነት ባህርይ ያላቸው ቋንቋዎች ለስመ-ተጸውኦ ብቻ የሚያገለግሉ ነባር ቃላተ-ስም (Proprail Lemmas) ጭራሹኑ የሏቸውም፣ ወይም በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በአፍሮ እስያዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ ይህ አይነት ስም አወጣጥ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ያለ ስለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ የሚገኙ ስሞች ማስረጃ ናቸው፡፡ በቅዱሳት መጻህፍቱ ውስጥ ያሉ የቦታና የሰው ስሞች ከሞላ ጎደል የየራሳቸው ፍች አላቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የቃላተ ስሙ ፍች ስም አውጪዎች ለተሰያሚው ሰው፣ ቦታ ወይም አካል ያላቸውን ስሜት፣ ሐሳብ ወይም ግንዛቤ የሚገልጹበት ነው፡፡

ስመ-ተጸውኦ ፍች አለው የሚለውን ጽንፍ የሚደግፉ ምሁራን ፍችን ከዚህ በላይ በገለጽነው መሠረት ከተረዳነው ስመ-ተጸውኦ ፍች ይኖረዋል ብለው ይከራከራሉ፡፡ ይህን ተከትሎም ስመ-ተጸውኦ ብዙ አይነት ፍችዎች ሊኖሩት ይችላል ይላሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹንም የቃላተ-ስም ፍች (meaning of name lemmas)፣ ዘውጋዊ ፍች (Categorial meaning)፣ ተቆራኝ ፍች (Associative meaning) እና ስሜታዊ ፍች (Emotive meaning) ብለው ይዘረዝሯቸዋል (Nyström፣ 2016፡40-52)፡፡ የቃላተ-ስም ፍች ማለት አንድ ቃል ለአንድ ነጠላ ቁስ/ነገር/ቦታ/ሰው ወዘተ. ስመ-ተጸውኦ ተደርጎ በሚወሰድበት ጊዜ የነበረው ፅንሰ ሐሳባዊ ፍች ነው፡፡ ዘውጋዊ ፍች በአንድ ስም የተጠራው አካል ከምን/ከማን ወገን እንደሆነ የሚጠቁም ፍች ነው፡፡ ዘውጉ ቦታ፣ ሰው፣ ወንዝ፣ ቁስ፣ ክስተት ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ ተቆራኝ ፍች የሚባለው ደግሞ አንድ ስም ሲጠራ አብሮ ሊታወስ የሚችልን ተደራቢ ፍች ያመለክታል፡፡ ስሜታዊ ፍች አንድ ስም በአድማጩ አእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው መጥላት/ መውደድ፣ መኩራት፣ማፈር፣ የመጨነቅ/ የመዝናናት፣ የድንጋጤ/ የመረጋጋት ወዘተ. ስሜት ነው፡፡

ይህ ጥናት የአባይን ስሞች ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የስመ-ተጸውኦ ፍች ዘርፎች አንጻር ይተነትናል፡፡ በመግቢያችን ላይ እንደተጠቀሰው፣ የጥናቱ አላማ የአባይን ስሞች ከሰያሚዎቹ ታሪክ፣ ባህልና የስም አወጣጥ ሥርዓት አንጻር መመርመር ነው፡፡ ዐባይ የሚገኘው በዋናነት የአፍሮ እስያዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሆኑ ህዝቦች ምድር ነው፡፡ እነዚህ ህዝቦች ደግሞ ስመ-ተጸውኦ ሲያወጡ ስለተሰያሚው ነገር ያላቸውን ስሜትና ግንዛቤ ሊገልጹላቸው የሚችሉ ፍች አዘል ቃላትን በመጠቀም ነው፡፡ በመሆኑን የአባይ ስሞች ሆነው ከጥንት እስከዛሬ የተሰጡ ቃላት የትመጣቸው ምንድነው? ምን ምን ፍች ተሸክመዋል? የየትመጣና የፍች ትንተኔዎች ምን ያሳዩናል? አሁን በጥቅም ላይ ያሉት የዐባይ ስሞች በተለይ በሀገራችን ምን ምን ስሜት ተደርቦባቸዋል? የሚሉትን ይመረምራል፡፡

### 3. የአባይ ስሞች የትመጣ፣ የቃለ ስምና ዘውጋዊ ፍች

አስቀድሞ እንደተጠቀሰው አባይ ስመ ብዙ የሆነ ወንዝ ነው፡፡ እነዚህ ስሞች ወንዙ ከጥንታውያን ግብጽ ጀምሮ እስከዛሬ በየዘመኑ ይጠራባቸው የነበሩና የሚጠራባቸው ስሞች ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች የነዚህን ስሞች የትመጣና ፅንስሀሳባዊ ፍች እንዳስሳለን፡፡ በ፬ ሥር የአባይ ጥንታዊ ስሞች፣ በ፬ ሥር ደግሞ የአባይ ዘመነኛ ስሞች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.1. የአባይ ጥንታዊ ስሞች

አባይ ከዚህ በፊት ሃፒ/ሃቢ (Hapi/Habi)፤ አር/አውር (Ar/Aur)፤ ፒሮ/ፊያሮ/ኢትረው (Piyaro/Fiyaro/Itrw) (Hillel 2005፣ Damtew 2016)፣ ሢሆር/ሺሆር (Shihor) (1ኛ ዜና መዋ. 13፡5)፤ የሚባሉ ስሞች እንደነበሩት የተለያዩ መዛግብት ያስረዳሉ። እነዚህ ስመ-ቃላት የተለያዩ ትመጣዎችና ፍችዎች አሏቸው። እየንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመለከታለን፡

ሃፒ ከሌሎች ስሞች ሁሉ ቀድሞ አባይ ይጠራበት የነበረ ስም ነው። ሃፒ/ሃቢ ስለሚለው ስም የትመጣ ሁለት አይነት ሐሳቦች አሉ። አንደኛው ከአባይ ውሃ ሙላት ጋር የተያያዘ ነው (Hillel, 2005: 33)። ሃፒ/ሃቢ በጥንታውያን ግብጾች አባይ እንዲሞላ የሚያደርግ አምላክ ስም ነው። ሃፒ/ሃቢ የሚኖረው በአባይ ምንጭ ውስጥ ባለ ዋሻ ነው። በየአመቱ የውሃውን ሙላት ይዞ ይመጣል ። ሃቢ/ሃፒ የፀሐይ አምላክ የሆነው የሆሩስ፣ የመሬት አምላክ *ጌብ* እና የእህል አምላክ *ነፈር* ጓደኛም ነው። ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ (2000፡ xiv) በግብጽ የሚገኘውና በድንጋይ ላይ በተቀረጸው የሃፒ ሀውልት ላይ «የአምላኮች አምላክ፣ የእህል ዘር አባት፣ የህይወት ምንጭ፣ነፍስ የሚዘራ፣ ከመከራ የሚፈውስ፣ ጎተራዎችን አሟልቶ፣ አትረፍርፎ የሚተው» የሚል ጽሑፍ ተጽፎበት እንደነበር ቤሳንኮን (1957) ጠቅሰው አስፍረዋል። ስሙ ምናልባትም ቀስ በቀስ እየተለወጠ የወንዙ መጠሪያ ሳይሆን አልቀረም።[3]

Encyclopedia Britanica (2016) ደግሞ ሃፒ/ሃቢ የሚለውን ቃል ፍች *ምሥጢራዊ* ወይም *ሰውር/ድብቅ* ከሚል *ሥርወቃል* ጋር ያጣቅሰዋል። ለጥንታውያን ግብጾች የወንዙ ምንጭ ምሥጢር ስለሆነባቸው በዚህ ስም ሳይጠሩት እንዳልቀሩ ይገመታል።

*አር/አውር* የሚለው ስም ጥንታውያን ግብጾች በቅብጥ ቋንቋ አባይን ይጠሩበት የነበረ ስም ነው (Hillel 2005: 88፣ Damtew 2016: 25)። የቃሉ ፍችም *ጥቁር* ማለት ነው (Hillel 2005፡ 88)። ሢሖር የሚለው ስምም በእብራይስጥ የተሰጠ ሲሆን ፍችውም *ጥቁር* ማለት ነው። የቅብጡን ቃል በመተርጎም የተገኘ ነው። ዘመናዊ ግብጻውያን ጸሐፍት ደግሞ ሢሖርን *ሺ-ት-ሆር* (shi-t-Hor) "The canal of Horus) *የሆሩስ ቦይ* ወይም *ሺ-ሁር* (shi-hur) *ቅዱስ ሐይቅ* ማለት ነው ብለውም ይፈቱታል (Rizk 1999-2000)።

ብዙ ጸሐፊዎች ለአባይ *ጥቁር* የሚል ፍች ያለው ስም የተሰጠው ከኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች በሚወስደው ደለል (አፈር) ቀለም አማካኝነት ነው የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ (Hillel 2005፤ Encyclopedia Britanica 2016)። ሆኖም ጉዳዩን ሰፋ አድርገን ስናየው የዐባይ ጥቁርነት ከወንዙ ደለል ቀለም ያለፈ ነው። በጥንታዊ የኢትዮጵያ ጥናት የታወቁት ፀጋዬ ገብረ መድኅን

---

[3] ሃፒ የሚለው ስም አባይ ከሚለው ስም ጋር ተቀራራቢ ድምጸትም ፅንሰ ሐሳብም አለው። ሃፒ ከአበይ ሙላት ጋር የተያያዘ ነው፣ አባይ ማለት ደግሞ ትልቅ ማለት ነው። የሁለቱ ቃላት ምንጭ አንድ ይሆን? ምናልባት ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከተገኘ ጥንታውያን የካም ህዝቦች ለዐባይ የሰጡትን የመጀመሪያ ስም ጠብቀው የቀሩት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይችላል።

(1990) እንደሚሉት ጥንታውያን ግብጾች የካም ልጆች ነበሩ[4]፡፡ ካም ማለትም ጥቁር ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጥቁር ህዝቦች በእብራይስጥ ኩሽ፣ በግሪክ ኢትዮጵ ይባሉ ነበር፡፡ ሁሉም ጥቁር ማለት ናቸው፡፡ እነዚህ ህዝቦች ሰፍረውበት የነበረውን የአባይ ሸለቆ ደግሞ *ከመት*[5] (ጥቁር አገር) ብለው ሰይመውት ነበር፡፡ ይህን አሰያያም ተከትለን ስንሄድ ጥንታውያን የካም ህዝቦች ሠፍረውበት የነበረውን ታላቅ ወንዝ ልክ እንደራሳቸውና እንደሀገራቸው ወንዛቸውንም «ጥቁር ወንዝ› ብለው ሰየሙት የሚለው ሐሳብ ውሃ ያነሳል፡፡ በዚህ መሠረት የአባይ ጥቁርነት ወንዙ የጥቁር ህዝቦች ንብረት መሆኑን የሚመሠክር እንጂ የደለል መልክ/ቀለም አመልካች አይደለም፡፡

ፒያሮ/ፊያሮ/ኢትረው[6] ለሚለው ስም ሁለት የተለያዩ ፍችዎች ተሰጥተውታል፡፡ አንደኛው «ታላቁ ወንዝ» የሚል ነው፡፡ የስሙ ምንጭ በጥንታዊ ቅብጥ itr ‹ወንዝ› የሚለው ቃል ነው፡፡ ቃሉ በኋለኛቹ የሳዲክና የቡሃሪክ ዘዬዎች ታላቅነትን የሚያመለክተው ቅጥያ ‹-o› ተጨምሮበትና የድምጽ ለውጥ ተካሂዶበት፣ በሳዲክ ዘዬ eiepo (eiero)፣ በቡሃሪክ ዘዬ ደግሞ iapo (iaro) "ታላቅ ወንዝ" የሚለውን ፍች አስገኘ፡፡ በመጨረሻም ስመተጸውኦ መሆኑን ለማመልከት "p/phi-" የሚል ቅጥያ ጨምሮ Pi-aro/ph-iyaro "ታላቁ ወንዝ" የሚለውን ፍች አስገኘ (Černý 1976: 48፣ Azevedo 2013፡ 26)፡፡

የዚህ ስም ፍች *ሃፒ* ከሚለው ስም ፍች እና ከዚህ በታች ከምናየቸው *ኣባይና ናይል* ከሚሉ ስሞች ፍች ጋር ተያያዥ ነው፡፡ በመሆኑም አንዱ የሌላው ትርጉም ናቸው ማለት ነው፡፡ የፒያሮ/ፊያሮ በኋለኛው ቅብጥ ዘዬ የነበረ የሃፒ/ሃቢ ትርጉም ሲሆን፣ ናይል ደግሞ የፒያሮ/ፊያሮ ሴማዊ ትርጉም ነው ማለት ይቻላል፡፡

የአባይ ጥንታዊ ስሞች አሁን ካሉት ዐረብ ግብጻውያን ጋር የሚያገናኛቸው ምንም ጉዳይ የለም፡፡ የአሁኖቹ ዓረብ ወይም ቀለመ ቀይ ግብጻውያን በየዘመናቱ ከአፍሪካና ከእስያ እየፈለሱ የመጡና ነባር ጥቁር ህዝቦችን አጥፍተው ምድሪቱን ወርሰው የቀሩ ናቸው (Williams 1974)። በተለይም የአሁኖቹ ዓረቦች በሐገሪቱ የሠፈሩት በ7ኛው መቶ ክፍለዘመን የእስልምናን መስፋፋት ተከትሎ ነው (Williams 1974፡ 56-57)፡፡ አባይ በነዚህ ስሞች ይጠራ የነበረው እነሱ ወደምድሪቱ ከመስፈራቸው ከብዙ ዓመታት በፊት ነው፡፡ አባይን በጥንታዊ ስሞቹ ይጠሩት የነበሩት ህዝቦች ማንነት ሲመረመር በሐይማኖታዊም ይሁን በዘመናዊ ታሪክ ምንጮች ከአሁኖቹ ግብጾች ይልቅ ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ሐይማኖታዊውን ዘርፍ ተከትለን ስንሔድ ጥንታውያን ግብጾች የካም ልጅ የሆነው የሚዝራይም ልጆች ናቸው (ዘፍ. ምዕ. 10) ፡፡ *ምስር* የሚለው የሀገሪቱ ስም የመጣውም ከዚሁ ነው፡፡ ሚዝራይም የኢትዮጵያውያን አባት የሆነው የኩሽ ወንድም ነው፡፡ በዚህ እይታ ጥንታውያን ግብጾችና ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ናቸው፡

---

[4]ጥነታውያን የካም/ ኩሽ ህዝቦች ዛሬ የኩሽ ቋንቋዎችን ከሚናገሩ ህዝቦች ጋር ሊያምታታ አይገባም፡፡ እነዚህ ህዝቦች የዛሬዎቹን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ እንዲሁም በሱዳንና በሌሎቹ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች የሠፈሩ ህዝቦች ናቸው፡፡ የቀደምት ሥልጣኔ መሥራችነታቸው የታወቁና እስከግብጽ ድረስ ዘልቀው ይገዙ የነበሩ ናቸው፡፡ እነዚህን ህዝቦች በሚመለከት Tsegaye Gbre-medhin (1991)፣ ግርማ አውግቸው (2018)፣ አማን በላይ (2009)፣ Bonet (2019) ይመልከቱ፡፡

[5] የግብጽ የጥንተ ስም ነው፡፡:

[6]አንዳንድ ጸሐፊዎች እነዚህን ቃላት ከላይ ካየናቸው አውር/አር/ኢተረው ከሚሉት ቃላት ጋር ተመሣሣይ ፍች ይሰጧቸዋል፡፡ ለምሳሌ (Degefu, 2003) aur/ar እና Iaro የሚሉትን ቃላት አንድ አድርገው ነው የወሰዷቸው፡፡ ፍቻቸውንም ‹‹ጥቁር›› ብለው ነው የተረጎሟቸው፡፡

፡ ይህ የወንድማማችነት ስሜት በግብጽ የዓረባዊ ብሔርተኝነት ስሜት እስከጀመረበት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ እንደነበረ የታሪክ ምሁራን ያወሳሉ (Tsegaye Gebre-medhin 1991፤ Erlich & Gershoni 2000፤ Tefla 2000)፡፡

ሳይንሳዊ ታሪክን ተከትለን ስንሄድ ደግሞ ጥንታውያን ግብጾች ከደቡባዊ አባይ ሐይቆችና ወንዞች ምድር ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ20000 - 11000 ዓመተ ዓለም ወደ ኮም አምቦ ተፋሰስ የፈለሱ ህዝቦች ናቸው (Tsegaye Gebre-medhin፣1991)፡፡ እነዚህ ህዝቦች ጥቁሮች በመሆናቸው ራሳቸውን ካም (ጥቁር ህዝብ) ብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ምድራቸውንም ከመት (*ጥቁር ምድር)* ብለው የሰየሙ ህዝቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ህዝቦች በእብራይስጥ ኩሽ፣ በግሪክ ኢትየጵ ተብለው የሚታወቁ፣ የእኛ የኢትዮጵያውያን ቅድመ አያቶች ናቸው፡፡ *ኢትዮጲያ* ብለው *መጀመሪያ* የመሠረቱት ታላቅ የጥቁር ህዝቦች ስልጡን ግዛት የዛሬዋን ግብጽንም ያካትት ነበር (Houston 1926፣ Williams 1974)፡፡ *ሥርዓተ ጽህፈትን*፣ *ምህንድስናን*፣ *ሥነ-ሕንፃን* እና *ሥነጥበብን* ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓም ያስተዋወቁ እነዚህ ህዝቦች ናቸው (Williams 1974:34)። እንደ ዊልያምስ አባባል፣ የዛሬዋ ኢትዮጵያ፣ በየዘመናቱ ሲቆረስና ሲነጠል የኖረው የጥንቱ ገናና የጥቁር ግዛት ኢትዮጵያ፣ ቅሪት ብቻ፡-

> For the Ethiopian empire once extended from the Mediterranean north and southward to the source of the Nile in the country (Abyssinia) which recently reverted to the ancient name of the Ethiopian empire of which in earlier times it formed its southeastern provinces. Even as late as the times of Menes, 3,100 B.C., Ethiopia still included three-fourths of Egypt …[7]. (Williams 1974:44)

> ከነዚህ ሁለት ማስረጃዎች አንጻር ሲታዩ ነው ጥንታዊ የአባይ ስሞች ከአሁኖቹ ግብጻውያን ጋር የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለ ግልጽ የሚሆነው፡ ፡ ስሞቹ በጥንታውያን ኢትዮጵያውያን የተሰጡ ነበሩ፡፡ የዛሬዎቹ ግብጻውያን፣ ጥንታውያን ካማውያን (ኢትዮጵያን) *ከመት (ጥቁር ምድር)* ብለው የሚጠሯትን ምድራቸውን፣ *አር/አውር)* (ጥቁር ውሀ) ብለው የሚጠሩን ወንዛቸውን ወርሱ ሲቀሩ፣ የወንዙ ግን ያኔ ይነገሩ የነበሩ ቋንቋዎች መነገር ሲጀምሩ አብረው ጠፉ፡፡

### 3.2. የአባይ ዘመነኛ ስሞች

በአሁኑ ጊዜ አባይ በሀገራችንና በመላው ዓለም የሚታወቅባቸው ሦስት ስሞች አሉ፤ አባይ፣ ግዮንና ናይል የሚባሉት፡፡ እነዚህ ሦስት ስሞች በአንድ ላይ የአባይ መጠሪያ ተገርገው እያገለገሉ

[7] የኢትዮጵያ ግዛት በአንድ ወቅት ከሰሜን ሜዲትራኒያን ጀምሮ የጥቁር አባይ ምንጭ እስከሆነችውና የጥንቷ ኢትዮጵያ ደቡባዊ ክልል እስከነበረች፣ ዛሬ ስሟን ኢትዮጵያ ብላ ወደ ጥንቱ ታላቅ ግዛት ስም እስከቀየረችው ሀገር(አቢሲኒያ) ይደርስ ነበር፡፡ እስከ ቅርቡ የመነስ ዘመነ ግዛት፣ 3100 ዓመተ ዓለም፣ ኢትዮጵያ የግብጽን ሦስት አራተኛ ታጠቃለል ነበር…፡፡

*ያሉት በኢትዮጵያ ብቻ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው ዓለም በሙሉ ናይል በሚለውን ስም ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ የነዚህን ስሞች የትመጣና ፅንሰሃባዊ ፍች ደግሞ ከዚህ ክፍል እንዳስሳለን፡፡*

አባይ/ዐባይ የሚለውን ስም በሚመለከት ሦስት አይነት የትመጣዎች አሉ፡፡ የትመጣዎቹና ፍችዎች የወንዙን ስም በአልፋው ‹አ› ወይም በዐይኑ ‹ዐ› ከመጻፍ ጋርም የተያያዙ ናቸው፡፡ ከአባይ ጋር ከተያያዙ የትጣዎች አንዱ *ሳባይ* የሚለው ስም « አባ እይ» ከሚሉ ሁለት ቃላት እንደመጣ የሚገልጸው አፈ-ታሪክ ነው፡፡ አፈ-ታሪኩ ከአባይ መነሻ በሆነችው ሰከላ አካባቢ የሚነገር ነው፡፡ አባይ የሚመነጨው ሰከላ ከሚገኘው የአቡነ ዘርአብሩክ ጠበል ነው፡፡ አቡነ ዘርአብሩክ በ8ኛው መቶ ክፍለዘመን መጨረሻ ክርስትናን እያስተማሩና ጠበል እያጠመቁ ሃይማኖታዊ ግብር ይፈጽሙ የነበሩ አባት ናቸው፡፡ በአካባቢው ሲያስተምሩ ሳለ፣ በወቅቱ ከሳቸው ጋር አለመግባባት የነበራቸው ሰዎች ለንጉሱ ‹መነኩሴው ለንጉስ አትገዙ እያሉ ያስተምራሉ» የሚል ወሬ ያደርሷቸዋል፡፡ ንጉሡም አቡነ አርአብሩክን ይዘው ያመጡላቸው ዘንድ ወታደሮችን ይልካሉ፡፡ መነኩሴው ሰከላ ላይ እንዳሉ ወታደሮች ሊወስዷቸው ሲመጡ፣ «መጽሐፎቼን ሁሉ እስከምመጣ ድረስ ጠብቀሽ እንድታቆይኝ አደራ ሰጥቼሻለሁ» ብለው ወደ ምንጩ ውሃ ይወረውሩና ይሄዳሉ፡፡ አምስት ዓመት ታሥረው፣ ሁለት ዓመት በየሀገሩ እየዞሩ ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ በሰባተኛው ዓመት ረዳታቸው ከሆኑ አባ ዘሩፋኤል ከሚባሉ መነኩሴ ጋር ይመጡና ምንጯ ጋ ሲደርሱ "ሰጠሁሽን አደራ ስጪኝ "ግሽ" ማለትም "ትፊ" ይላሉ፡፡ ይህን ጊዜ ከሰባት ዓመት በፊት ወደምንጩ የወረወሯቸው መጻሕፍት በሙሉ ከውሃው ውስጥ ይወጣሉ፡፡ አቡነ ዘርአብሩክም አብረዋቸው ለነበሩት መነኩሴ "አባ እይ፣ ይህን ተአምር" ብለው ተናገሩ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላም *ግዮን* ይባል የነበረው ወንዝ ምንጭ "ግሽ" እና "አባ እይ"ን በማዋሃድ "ግሽ አባይ " ተባለ ይላል፡፡ ወንዙ ደግሞ አባይ ተብሎ ቀረ የሚል አፈ-ታሪክ ነው፡፡

በአገውኛ 'ግሽ' ማለት "ቆፍር" ማለት ነው፡፡ "ግሽ አባይ" ደግሞ "አባ ቆፍር" ተብሎ ሊፈታ እንደሚችልም Oestigaard and Gedef (2011) ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህኛው ጋር ተያያዥ የሆነ አፈ-ታሪክ ግን የለም፡፡

ሁለተኛም አባይ "አባዊ" ከሚለው ቃል ተገኘ ይባላል (ደስታ፣ 1962፡ 75) ፡፡ እንዲህ ተብሎ የተጠራውም አባይ ብዙ ወንዞችን የሚያስገብርና በጣም ረጅም መንገድ የሚጓዝ፣ ከወንዞች ሁሉ የበለጠ በጣም ግዙፍና የወንዞች ሁሉ አባት መሆኑ ነው፡፡

*ዐባይ* (በዐይኑ 'ዐ' መጻፉን ልብ ይሏል) የሚለው ስም ደግሞ "ዐበየ" ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተመሠረተ ነው፡፡ "ዐባይ" የሚለው ቅጽል "ትልቅ" ማለት ነው፡፡ ይህም በአንስታይ ጾታ ሲነገር ነው፣ በተባእታይ ሲሆን «ዐቢይ» ይሆናል፡፡ ዐባይ ከወንዞች ሁሉ የላቀ ትልቅ መሆኑን ለማጠየቅ የተሰጠው ስም ነው፡፡ በአንስታይ ስመ መጠራቱ ከተለመደው ተባዕታይ ጾታ የተለየ ቢመስልም ወንዞችን በሴት ስም መጥራት ነባር ባህል እንዳለን ግን ማስረጃዎች አሉ፡፡ ይህም ወንዞችን ግልገልና እናት ብሎ የመጥራት ልማድ ይገለጻል፡፡ ግልገል በለስ፣ ግልገል ጊቤ የመሰሉ ወንዞች

እንዳሉን ሁሉ፣ አንዳንድ ጊዜ ግልገል የሚባለው ውንዝ የሚገብርለትን ሌላ ወንዝ *እናት* ተብሎ በእንስታይ ጾታ ይጠራል፡፡ ግልገል ጨዪ እና እናት ጨዪ[8] ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

በአጠቃላይ አባይ/ዐባይ ከሚለው ጋር ተያይዞ የሚነገሩት የት መጣዎች የስሞችን ምንጭ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች (አማርኛ፣ ግእዝ፣ አገውኛ) ያደረጉ ሲሆን፣ ፍቻቸው ደግሞ ከወንዙ ትልቅነት እንዲሁም ከክርስትና ሀይማኖት ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ የትመጣቸውም ሆነ በፍቻቸው ፍጹም ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ ሆኖም የአባይ ፍች ከጥንታዊ የወንዙ ስሞች አንጻር ሲታይ ተያያዥነት አለው፡፡ አባይ በድምጸቱ በo ከተገለው ሃፒ/ሃቢ፣ በፍችው ደግሞ ከፒያሮ/ፊያሮ/ኢትርው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ የአባይ ድምጸትና ፍች ከጥንት የወንዙ ስሞች ጋር መሳሰል፤ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ ጥንቱን ስም ጠብቀው መኖራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ግዮን አባይ ወንዝ *አባይ/ዐባይ* ከመባሉ በፊት ይጠራበት የነበረ ስም ነው ፡፡ ይህ ስም ብዙ ጊዜ የእብራይስጥ ቃል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ፍችውም መፍለቅለቅ፣ መመንጨት ወይም ግንፍል ብሎ መውጣት የሚል ነው (Butler 1991)፡፡ ደስታ ተክለወልድ(1962)[9] እና ኪዳነወልድ ክፍሌ ግዮንን እንደ ግዕዝ ቃል ይቆጥሩታል፡፡ ለምሳሌ ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፣ 312-313) ቃሉ በእብራይስጥ ጊሖን፣ በጽርእ ጌዖን እንደሚባል ጠቅሰው *ግዮንን* እንደ ግእዝ ቃል ቆጥረውታል፡፡ ለግዮን በሰጡት ፍችም ከእብራይስጡ ጋር የሚስማማ ነው፡- «የሐውር በኀይል ወይርዕም ወድምፅ ማዩ ዐቢይ ወግሩም ማለት ነው፡፡ የውሃውን ብዛት የመልካውን ስፋት ያካሄዱን ኀይል፣ የጩኸቱን ግርማ ፏፏቴውንና ተመማሙን ድምጡ እንደነጐድጓድ መኾኑን ያሳያል።» በማለት ገልጸውታል፡፡ ስሙ በሦስቱም ቋንቋዎች ከመገኘቱ ባሻገር ግን በቀዳሚነት የምን ቃል እንደሆነ የሚያሳይ ጠንካራ ማስረጃ የለም፡፡ በርግጥ በእብራይስጥ ከአባይ ሌላ ግዮን በሚል ስም የሚጠራ ምንጭ አለ፡፡[10] ሆኖም ይህ ብቻውን የስሙን የትመጣ እብራይስጥ ያደርገዋል ወይ የሚለው አጠያያቂ ነው፡፡ ምክንያቱም ለዚሁ ቃል ዘመድ (ምንጭ) ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችም ይገኛሉ፡፡ እንደ ጐሐነ[11]፣ *ጎዮ*[12] ፣ *ጐሀ*[13]፣ *ጎሸ*[14]፣ ተንጓጓ ያሉ ቃላት አሁንም በቋንቋዎቻችን አሉ፡፡ በተጨማሪም ስያሜው በአብዛኛው መዛግብትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ግን አስካሁን የአባይ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ የሚገኝ ነው፡፡ በተለይም የዐባይ ምንጭ በሆነችው ሰከላ ደግሞ አሁንም ተዘውታሪ የወንዙ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ እንዳለ በመስክ ጉብኝት ወቅት የታዘብኩት ሀቅ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ገዮነ የመለው ስም ምንጭ ኢትዮጲያ ሊሆን ይችላል የሚለውን ሐሳብ ያጠናክራል፡፡

---

[8] ሁለቱ ጨዪዎች በምሥራቅ ጎጃም እናርጅ እናውጋ ወረዳ የሚገኙ ወንዞች ናቸው፡፡

[9] ደስታ ተክለወልድ (1962፡255) ግዮን ለነጭ አባይ ብቻ የሰጠ ስም እንደሆነ ነው የሚገልጹት፡፡

[10] (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት, 1980)

[11] ጐሐነ (ተንጓጓ) (ግእዝ) (Leslau, 1991, p. 207)

[12] ጐየ (ሸሸ)፣

[13] ጐሀ (ወጣ)፣ ሴማዊ ሥርወቃል gawah 'to dawn', *g.wh* 'dawn' ፣ እብራይስጥ፡ *gắḥ* (gwh, *gyh)* 'burst forth' (Leslau, 1991, p. 207)

[14] ደፈረሰ (አማርኛ)

*ናይል* የሚለው ስም በአሁኑ ወቅት አባይ በመላው ዓለም የሚታወቅበት ስም ነው፡፡ በዓረብኛም ከዚሁ ጋር ተያያዥ በሆኑ *አል-ኒል* (Al-Nil)፣ *ባሕር አል-ኒል* (Bahr Al-Nil)፣ *ናሕር አል-ኒል* (Nahr Al-Nil) በሚባሉ ስሞች ነው የሚጠራው፡፡

*ናይል* የሚለው ስም የትመጣና ፍች እስካሁን እያከራከረ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ቃሉ በጥንታዊ የግሪክ *ሥነጽሑፍ ሥራዎች* ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ የሚገኝ ስም እንደሆነ፤ የግሪኩ ቃል (Neilos)፣ በላቲን ኒሉስ (Nilus)፤ ቀጥሎም በእንግሊዝኛ ናይል (Nile) እንደተባለ ይነገራል (Degefu 2003: 3)፡፡ ሆኖም ግሪክ ከየት አመጣው ሲባል ሁለት አከራካሪ ሐሣቦች ይሰነዘራሉ፡፡ አንደኛው አውሮፓ ተኮር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አፍሪካ ተኮር ልንላቸው እንችላለን፡፡ አውሮፓ ተኮሩ መላምት *ናይል* የሚለው ቃል (1ኛ) በጥንታዊ ግሪክ የፖታሞይ (የወንዝ አማልእክት) የነበሩት የኦሽነስና ቴትይስ ወንድ ልጅ ስም ነው፤ (2ኛ) ከማይታወቅና ምናልባትም በሳንስክሪት *ኒላ* (Nila) "*ሰማያዊ*" ከሚል፣ ወይም በአባይ ወንዝ ከምትበቅል አበባ የተገኘ ስም ነው የሚል ነው (Hillel 2005: 88)፡፡

በመሠረቱ ጥንታውያን ግሪኮች *ናይል* የሚለውን ስም እራሳቸው የሰጡት ሳይሆን በወንዙ ዙሪያ ከኖሩ ህዝቦች የወሰዱት ነው፡፡ ይህን ለመረዳት የጥንታውያን ግሪኮችንና ግብጾችን[15] ግንኙነት መመርመር ያሻል፡፡ የጥንታውያን ግሪኮች ስልጣኔ በቀጥታ ከጥንታውያን ግብጾች የተወረሰ ለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡[16] የአባይ ሀተታ ሳይቀር ከጥንታውያን ግብጾች የተኮረጀ አንጂ አዲስ ፈጠራ አይደለም፡፡ ኒሉስ የሚለው የአባይ ስም ተደርጎ የሚወሰደው ከጥንታዊ ግብጽ ሃተታ ተፈጥሮ (ሚቶሎጂ) የተቀዳ ነው፡፡ ኔሎስ በግሪክ የውሃ አማልክት የሆኑት ኦሽነስና የቲተየስ ልጅ ነው፡፡ በጥንታውያን ግብጾች ደግሞ ሃፒ/ሃቢ የሆሩስ (የፀሓይ አምላክ) ልጅ እና የመሬት አምላክ (ግብ) እና የእህል አምላክ (ንፈር) ጓደኛ ነው፡፡ በአጭሩ የግሪኮች ኔሎስ ከጥንታውያን ግብጾች ሃፒ/ሃቢ የተቀዳ ሀተታ ነው፡፡ ኔሎስ የግሪክ ነው ቢባል እንኳን ዋናው የሚቶሎጂው ምንጭ ጥንታውያን ግብጾች መሆናቸው እሙን ነው፡፡

በሌላ በኩል ስናየውም፣ ክፍል 0 ስለ ስመ-ተጸውኦ ፍች በተመለከትነው መሠረት፣ በአውሮፓውያን ባህል በብዛት የቦታ/ወንዝ ስመ-ተጸውኦ ሲሰጥ በቋንቋዎች ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ፍች አዘል ቃላት ከመምረጥ ይልቅ፣ ለስምነት ብቻ በሚያገለግል ቃል መሰየም ነው የተለመደው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ በየሀገሮቹ ያሉ የቦታ ስሞች ከስምነት የዘለለ ፍች የሌላቸው፡፡ ስለዚህም ናይልን ብቻ ከባህላቸው ነጥለው ፍች ባለው ቃል የሚሰይሙበት ምክንያት አይኖርም፡፡

አፍሪካ ተኮር የሆነው የናይል ደግሞ *ናይል* የሚለው ስም *ነሃል* (nahal) "*ወንዝ*" ወይም "*ሸለቆ*" ከሚለው የሴማዊ ቃል ተገኘ የሚል ነው፡፡ ይህ ቃል በአረብኛ *ናህሩን* (nahrun)፣ በእብራይስጥ *ነሃር/ነሃሮት* (nehar/neharot)፣ በአማርኛና በግእዝ *ባሕር* (bahr) ለሚሉት ቃላት እናት ቃል

[15] በንዑስ ክፍል 0 በተመለከትነው መሠረት፣ ጥንታውያን ግብጾች የታላቋ ገናና ጥንታዊ ኢትዮጵያ አካል ነበረች፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት የWilliams (1974)ን በተለይም ምዕራፍ 2፣ "Ethiopia's Oldest Doughter: Egypt" የሚለውን ይመልከቱ፡፡

[16] See for example Saakana, A.S (ed.) (1991) African Origins of Major World Religions. London: Karnak House. The Greek mythology was highly influenced by the Egyptian Mythology.

ነው፡፡[17] ይህ ፍች ጥንታውያን ግብጾች (የካም ህዝቦች) ወንዙን ይጠሩባቸው ከነበሩ ስሞች ፒያሮ/ፊያሮ/ኢትርው ከሚሉት ፍች ጋር ይዋረሳል (ዐን ይመልከቱ)፡፡ በመሆኑም ናይል የሚለው ስም የወንዙን ጥንታዊ ስሞች በሴማዊ ቋንቋ በመተርጎም የተገኘ መሆኑን ስለሚያስመሰክር ከላይኞቹ መላምቶች የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መልክ ስምን እየተረጐሙ መጥራት ደግሞ የተለመደ ነበር፡፡ ለምሳሌ ካም (ጥቁር) ብለው ራሳቸውን የሚጠሩትን ህዝቦች፣ እብራይስጦች ኩሽ (ጥቁር)፣ ግሪኮች ኢትዮጵ (ጥቁር) እያሉ በየቋንቋቸው ተርጉመው ይጠሯቸው ነበር (ፀጋዬ፣ 1990)፡፡

የአሁኖቹ ዐረብ ግብጻውያን ግን *ናይል* የሚለውን ስም የትመጣ ከአጠቃላይ ሴማውያን ቋንቋዎች ይልቅ ወደ ዓረብኛና ወደአሁኗ ግብጽ ታሪክ ለመጐተት ጥረት ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ለአብነትም ሪዝቅ የተባሉ ጸሐፊ አል አህራም ተብሎ በሚታወቀው የግብጽ ጋዜጣ እ.አ.አ ዲሴምበር 30፣ 1999- ጃኑዋሪ 5፣ 2000 ዓ.ም በታተመው ልዩ እትም የተለያዩ የግብጽ ጸሓፊዎችን ጠቅሰው ያሠፈሯቸውን መላምቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዛኪር የተባሉ ሰው *ናይል* የሚለውን ቃል ጥንታውያን ግሪኮች ከጥንታውያን ግብጾች ጋር ግንኙነት ከነበራቸው ሌሎች ህዝቦች እንደወሰዱትና የቃሉ ምንጭም የአረብኛው ነዋል (nawal) የሚለው ቃል ሊሆን እንደሚችል መጻፋቸውን ይገልጻሉ፡፡ ፍችውም *ስጦታ፣ በረከት* የሚል ነው[18]፡፡ ስያሜውም ወንዙ ለግብጻውያን ከፈጣሪ የተሰጠ ጸጋ/ ስጦታ መሆኑን ያመለክታል ሲሉ አስፍረዋል፡፡ አንድ ስሙ ያልታወቀ ፈላስፋን በመጥቀስም የወንዙ ስያሜ ኒሉስ (Nilus) ከሚባል የጥንታዊ ግብጽ ንጉስ ስያሜ እንደመጣ፣ ፕሊን (Pline) የተባለ ሮማዊ የታሪክ ተመራማሪ ደግሞ ወንዙ ከሚመነጨበት ኒሎስ ከተባለ የመሃል ሀገር ስም አንደተወሰደ መጻፋቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ አሕመድ ከማል ፓሻ የተባሉ ሌላ ምሁርን ጠቅሰው ደግሞ ቃሉ "ኒኑ" ከሚልና ጥንታውያን ግብጾች ወንዙን ለመጥራት ይጠቀሙበት ከነበረ ቃል መጣ ማለታቸውን ይገልጻሉ (Rizk, 1999-2000)፡፡ የቃሉን ፍችና ስያሜው መቼ ያገለግል እንደነበር ግን ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ሆኖም በተለይ *ናይል* የሚለው ስም ምንጭ ዓረብኛ ነው የሚለው መላምት Erlich & Gershoni (2000፡ 3) "...Scholars and observers of Egypt tended ... to relate the river to the Middle East, to the land of Islam, to the Mediterranean. They neglected its southern section, the Nile's backyard, almost entirely"[19] እንዳሉት የስሙን ምንጭ ለመንጠቅና ፍችውንም ለነሱ ብቻ የተሰጠ ስጦታ ወይም በረከት መሆኑን ለማስረጽ የሚያደርጉት ምኞታቸው አካል እንጂ ውሃ የሚያነሳ ማስረጃ የላቸውም፡፡ *ናይል* የሚለው ስም ዐረብኛ ወደምድረ ግብጽ ከመምጣቱ ከብዙ ዘመን በፊት ይጠራበት እንደነበር በጥንታዊ የግሪክ መዛግብት ሠፍሯል፡፡ ግሪኮች ደግሞ ከግብጽ

[17]ወልደጻዲቅ ደገፉ (2003፣ 3) አማርኛና ግእዝ የሴም ቋንቋዎች ቢሆኑም *ወንዝ* እና *ፈለግ* የሚሉ ቃላት ስሏቸው *ናይል* ለሚለው ስም ምንጭነት ከተጠቀሰው የአረብኛ ቃል *ናህር* የተለዩ ቃላት እንዳሏቸው ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ለአረብኛው አቻ የሚሆነው የአማርኛና ግእዝ ቃል *ባሕር* የሚለው ቃል ነው፡፡ ባሕር በግእዝ ትልቅ ወንዝ ተብሎ ይፈታል፡፡ (ኪዳነወልድ 1948፡ 261) (Leslau, 1991, p. 93)፡፡ በአማርኛም ቢሆን የወንዝ አካል የሆነና ሰፋ ያለ ውሃ ባህር ይባላል፡፡

[18] እንዲሁም ኃይሉ (2000፡ xiv) ይመልከቱ፡፡

[19] የግብጽ ምሁራንና አጥኚዎች፣ ወንዙን ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከእስላም ምድር እና ከሜዲዲራንያን ጋር የማያያዝ ዝንባሌ አላቸው፡፡ ደቡባዊ ክፍሉን፣ የናይልን ያኃላ ደጀን፣ ሙሉ በሙሉ ዘንግተውታል፡፡

ጋር ግንኙነት የነበራቸው ዐረብኛ ከመናገራቸው በፊት ነው፡፡ ስለሆነም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ7ኛው መቶ ክፍለዘመን ወደግብጽ የገባው ዐረብኛ ቋንቋ የስያሜው ምንጭ ሊሆን አይችልም፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዘ አባይ በሦስት ስሞች እየተጠራ የሚገኘው በኢትዮጵያ ብቻ ነው፡፡ ከሦስቱ የአባይ ዘመነኛ ስሞች ሁለቱ ከጥንታዊ ስሞች ጋር የሚዛመዱ እንጂ አዳዲሶች አይደሉም፡ ማለትም ከጥንታውያን ኢትዮጵያውን ጀምሮ እስከዛሬ የዘለቁ ስሞች ናቸው፡፡ ግዮን የሚለውም ስም ቢሆን በአሁኑ ጊዜ የወንዙ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ ያለው ኢትዮጵ ውስጥ ብቻ በመሆኑ፣ እና የስሙ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በመገኘታቸው ኢትዮጵያዊ መልኩ የጎላ ነው፡፡ የአሁኖቹ ግብጻውያን የስሙን ሴማዊ መጠሪያ ከመገልገልና አለፍ ሲልም የስሙን ምነጭ ለመንጠቅ ከሚያደርጉት ጥረት ውጭ ለስሙ ፍችም ሆነ የትመጣ ያበረከቱት ነገር የለም፡፡ ዘመነኛ የአባይ ስሞችም፣ እንደጥንታወውያን ስሞች፣ ደንበኛ የኢትዮያውያን ስሞች ናቸው፡፡

### 3.3. የአባይ ስሞች ከኢትዮጵያውያን ስም አወጣጥና ባህል አንጻር ሲቃኙ

አባይ የዓለም ሥልጣኔ በተጀመረበት ቦታ የሚገኝ ወንዝ በመሆኑ በረዥም ዘመን ውስጥ የተሰጡት ስሞች በዝተውና ተመዛግበው መገኘታቸው አያስደንቅም፡፡ የነዚህ ስሞች የትመጣና ፍች ከወንዙ ጋር ለረጅም ዓመታት አብረው በኖሩት ህዝቦች ባህል፣ ቋንቋ፣የስም አወጣጥ ልማድ ላይ ተንተርሶ ሊደረግ ይገባል፡፡ በነዚህ ህዝቦች ቋንቋዎች/ባህሎች የቦታ (የወንዝ፣ የጋራ፣ የመንደር፣ የሜዳ ወዘተ.) ስመ-ተጸውኦ ሲሰጥ ከስመ ተጸውኦው በተጨማሪ የቦታውን ዘውግ (ጋራነት፣ ወንዝነት፣ ሸለቆነት፣ ሜዳነት) የሚገልጽ ቃል አብሮ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ከአራት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማለትም ከአማርኛ፣ ከኦሮምኛ፣ ከትግርኛና ሳሆ የተሰበሰቡ የቦታ ስሞች እንመልከት፡-

አማርኛ፡ ቦሩ ሜዳ፣ ደጋ ዳሞት፣ ጅብ ዋሻ፣ አዲስ ከተማ፣ አደባባይ ኢየሱስ

ኦሮምኛ፡ ጋራ ሙለታ (የሙለታ ኮረብታ)፣ ቱሉ ዲምቱ (ቀይ ተራራ)፣ ሆራ አርሴዲ (አርሴዲ ሐይቅ)፣ ለገዳዲ ( ዳዲ ወንዝ)

ትግርኛ፡ ግራ ካሡ (የካሡ እርሻ)፣ ጋበ ከረን ( ዳልቻ ተራራ)ሳሆ ፡ አሲምባ (አሳ እምባ) ( ቀይ ተራራ)

እነዚህ የቦታ ስሞች በስመ-ተጸውኦና በዘውግ ቃላት ጥምረት የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ቦታዎቹ እንዲህ ሲጠሩ ኖረው፣ ከዘመናት በኋላ ከጥምር ቃላቱ አንደኛው ጠፍቶ በአንደኛው ብቻ ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴ መግለጫው ጠፍቶ ስመ-ተጸውኦው ሲቀር፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ስመ-ተጸውኦው ጠፍቶ መግለጫው ብቻ የቦታው ስም ሆኖ ይቀራል፡፡ ለዚህ እንደማስረጃ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ቦታዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አዲስ አበባ እየሰፋች ስትመጣ አንዳንድ ቦታዎች መጀመሪያ በቦታው በነበሩ መለያ ምልክቶች (ቤት፣ሱቅ፣ሆቴል ወዘተ.) ይጠሩ ነበር፤ ወለቴ ሱቅ፣ ወሰን ግሮሰሪ፣ ናሆም ሆቴል፣ አያት መኖሪያ ቤቶች የሚባሉ ቦታዎችን ልብ ይሏል፡፡ ቀስ በቀስ ዘውጎቹ እየቀሩ መጡና አሁን ቦታዎች ወሰን፣ ወለቴ፣ ናሆም፣ አያት ተብለው መጠራት ጀምረዋል፡፡

መርካቶ (መርካቶ ኢንዲጂኖ)፣ መሳለሚያ (አማኑኤል መሳለሚያ?)፣መናኸሪያ (አውቶብስ መናኸሪያ) የሚሉት ደግሞ ዘውጎቹ ብቻ ስመ-ተጸውኦ የሆኑባቸው ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ዛሬ ብዙ ሆነው የሚታዩን የአባይ ስሞች በዚህ የስም አሰጣጥና ለውጥ ሥርዓት መሠረት ስንመዝናቸው በወጥነት የሚሄዱበት ስልት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአባይ ስሞች በተደጋጋሚ የምናገኛቸው ፅንሰ ሐሳቦች አራት ናቸው፡- ትልቅ፣ ጥቁር፣ ወንዝ እና ኀይለኛ/ገንፋይ፡፡ ምናልባትም ኃይለኛነቱን ከትልቅነቱ ጋር ካዋረስነው ሦስት ብቻ ይሆናሉ፡፡ ከነዚህ ሦስት ፅንሰ ሐሳቦች ሁለቱን ፅንሰ ሐሳቦች ማለትም የአባይን (ትልቅ) እና የናይልን (ወንዝ) ወስደን አንድ ላይ ብንጠራቸው "ልቁ ወንዝ" የሚለውን ስም ይሰጡናል፡፡ ይህ መጠሪያ ደግሞ በ0 እንዳየነው አንዱ የአባይ የጥንት ስም ነው፡፡ በመሆኑም የዛሬዎቹ *አባይና ናይል*፣ የጥንቱ ስያሜ በሴማዊ ትርጓሜዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ *ሂሆር* የሚለው ቃልም እንዲሁ ሴማዊ ትርጓሜ ነው፡፡ ሦስቱን ሴማዊ ቃላት በአንድ ላይ ስናጣምራቸው ደግሞ *‹‹ትልቁ ጥቁር ወንዝ››* የሚል ጥምር ስያሜ ይሰጡናል፡፡ ይህ ጥምር ስም በተለያዩ አካባቢዎች ሲጠራ ከዚህ በላይ በተገለጸው *መሠረት*፣ ስሙን በማሳጠር በአንዳንድ አካባቢዎች ዘውጉን (ተገላጩን) ብቻ፣ ሌሎች ደግሞ ገላጮችን ብቻ ይዘው በመቅረታቸው ዛሬ የተለያዩ ስሞች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልክ ሲታይ የናይል ስም አመጣጥ ከነባር ከአፍሮ እስያዊ ቋንቋዎች (በተለይም ከወንዙ ጋር በቅረበት ለዘመናት የኖሩት የጥንቶቹ ካማውያን እና ሴማውያን) የስም አወጣጥና የስም ለውጥ ውስጥ የሚገኝ እንጂ፣ በአውሮፓውያንና በዛሬዎቹ ዐረብ ግብጻውያን ጸሐፍት እንደሚባለው ከኢንዶ አውሮፓዊ ቋንቋዎች ወይም አሁን በግብጽ ከሚነገረው ዐረብኛ ብቻ የሚመዘዝ ሊሆን አይችልም፡፡

በዓባይ ስሞች የሚገለፁ ጽንሰ ሃሳቦችም ቢሆኑ የስሞችን አፍሪካዊነት የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ አባይ ስሞች በዋናነት የምናገኛቸው ፅንሰ ሐሳቦች አራት/ሦስት ናቸው ብለናል፡- ትልቅነት/ኀይለኛነት፣ ጥቁርነት እና ወንዝነት፡፡ ትልቅነት አንፃራዊ ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡ ዐባይን ትልቅ ወንዝ ብሎ ለመጥራት የግድ ከሌሎች ወንዞች ጋር ማነጻጸር ይሻል፡፡ ከዐባይ ጋር የሚነጻጸሩ ወንዞች በሌሉበት ዐባይን ትልቅነት የሚገልጽ ስም ማወጣት ከባድ ነው፡፡ ይህ እውነታ የዐባይን ትልቅነት የሚገልጸው ስም በዛሬዋ ግብጽ ላይ ብቻ ተወስነው ይኖሩ በነበሩ ህዝቦች ወጣ ማለት አያስደፍርም፣ የሚያነጻጽሩበት ሌላ ወንዝ የለምና፡፡ ስለዚህም የዚህ ስም ባለቤቶች ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን/የካም ህዝቦች ናቸው ለማለት ያስደፍረል፡፡

ሌላው የአባይ ጥቁርነት ነው፡፡ የዐባይን ጥቁርነት ብዙ ጸሐፊዎች ከኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች በሚወስደው ደለል ቀለም አማካኝነት የተሰጠው ነው የሚል ሃሳብ እንደሚያቀርቡ ቀደም ሲል በ0 ጠቅሰናል ፡፡ ሆኖም የዐባይ ጥቁርነት ጥንታውያን የካም ህዝቦች ሠፍረውበት የነበረውን ታላቅ ወንዝ ልክ እንደራሳቸውና እንደህገራቸው ወንዛቸውንም *ጥቁር ወንዝ* ብለው በመሰየማቸው የተገኘ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ስለዚህም የአባይ ጥቁርነት ወንዙ የጥቁር ህዝቦች ንብረት መሆኑን የሚመሠክር እንጂ የደለል መልክ/ቀለም አመልካች አይደለም፡፡

ሌላው ከዐባይ ስሞች የምናገኘው ጽንሠ ሐሳብ ኀይለኛ/ የሚገነፍል መሆኑን ነው፡፡ ይህ ፍች ግዮን ከሚለው ስያሜ የሚገኝ ነው፡፡ በመሠረቱ ዐባይ ሲገነፍልና በኃይል ሲጓዝ የሚታየው በላይኛው የወንዙ ተፋሰስ ነው፡፡ በታችኛው ተፋሰስ ጉዞው በርጋታና በፀጥታ ነው፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነት ስያሜ ሊሰጠው የሚችለው በላይኛው ተፋሰስ እንጂ በተችኛው ሊሆን አይችልም፡፡ ይህን ሐሳብ የሚያጠናክርልን በተለይ በመስክ ጥናት ያገኘሁት እውነታ ነው፡፡ ዓባይ ከሚለው ስም በፊት የወንዙ መጠሪያ ሆኖ ያገለግል የነበረው ስም ግዮን ነው፡፡ ስያሜው በአሁኑ ወቅት በጥንታውያን መዛግብትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ቢሆንም፣ በተለይ የዐባይ ምንጭ በሆነችው ሰከላ ግን እስካሁን ተዘወታሪ የወንዙ ስም ግዮን ነው፡፡ .

በጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ መጻሕፍት የካም ልጆች በግዮን ወንዝ ዳርቻ የሚፈጸም የንግስና ሥርዓት ዘርግተው ለረጅም ጊዜ፣ግብጽንም የሚያካትት፣ ኢትዮጵያ የሚል ሀገር መሥርተው መኖራቸውን ይገለጻል (Houston 1926፣ Williams 1974፣ ፀጋዬ 1990፣ Tsegay 1991፤ አማን 2009፣ Bonnet 2019)፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአባይን የመገንፈልና የኃይለኝነት ባህርይ ከማንም በላይ የሚያውቁት እነዚህ ጥንታውያን ኢትዮጵያውን ናቸው፡፡ ከመነሻው ጀምሮ በአብዛኛው በሚያልፍባቸው ቦታዎች ሁሉ አካሄዱን/ የኃይለኝነት፣ የመገንፈል ባህርይውን የነሱን ያህል ማንም ሊያውቀው አይችልምና፡፡ ስለዚህም ግዮን ለሚለው ስም የካም ልጆች (ጥንታውን ኢትዮጵያውያን) ያወጡት ስም ከመሆን አያልፍም፡፡ ስሙ ምናልባትም ወደእብራይስይ ተተርጉሞ፣ በውሰት ሄዶ ወይም የአፍሮ እስያ ቋንቋዎች የጋራ ሥርወቃል ሆኖ ሊሆን ይችላል፡፡ ከላይ እንደገለጽነው ከዚሁ ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ቃላት አሁንም በቋንቋዎቻችን አሉና፡፡

በአጠቃላይ የአባይ ስሞች ፍች የአካባቢውን ነባር ህዝቦች ታሪክ፣ ቋንቋና የስም አወጣጥ ባህሎችን መሠረት በማድረግ ሲተነተኑ የወንዙ ስሞች የትመጣና ፍች ከዓረብኛ፣ ከግሪክና ከሳንስክሪት ይልቅ ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን (የካም ልጆች) መሆናቸውን የሚመሰክሩ ናቸው፡፡

### 3. 4. ከአባይ ስሞች ጋር የተያያዙ ስሜታዊ ፍችዎች

በክፍል 0 እንደተገለጸው ስሜታዊ ፍች አንድ ስም በአድማጩ/በሰሚው አእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው መጥላት/ መውደድ፣ መኩራት፣ማፈር፣ የመጨነቅ/ የመዝናናት፣ የድንጋጤ/ የመረጋጋት ወዘተ. ስሜት ጋር ይያያዛል፡፡

እንዲህ አይነት ከስም ጋር የተያያዙ ስሜታዊ ፍችዎች ህዝቦች ለረጅም ጊዜ ከተሰያሚው ጋር ባላቸው ገጠመኝ ወይም ግንዛቤ ላይ የሚመሠረቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ለመለየት ያስቸግራሉ፡፡ በብዙ ጥናቶች እንዲህ አይነት ፍችዎች የሚለዩት ህብረተሰቡ ስሜቱን በሚገልጽባቸው ሥነቃሎችና የጥበብ ውጤቶች ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይ ከስሞች ጋር የተገናኘ ስሜት ስሞችን በተደጋጋሚ በመጠቀም ወይም ከመጠቀም በመታቀብ ሊገለጽ ይችላል፡፡

በሀገራችን አባይን የሚመለከቱ የሥነቃልና የጥበብ ውጤቶችን ከመረመሩ ጥናቶች መካከል Tefla (2000)፣ Damtew(2016)፣ Gebre (2011) ተጠቃሽ ናቸው ፡፡ በነዚህ ጥናቶች አባይ አሉታዊም አዎንታዊም ስሜቶች የተደረቡበት መሆኑ ተገጹዋዋል፡፡ አባይ እንደ ባዳ/እንግዳ፣ እንደ

ወዳጅ እና እንደ ጠላት (Damtew፣ 2016)፣ አባይ እንደብሔራዊ የማንነት ትእምርት (Tefla 2000፣ Gebre 2011)፣ አባይ እንደ በዳይ (Tefla፣ 2000) ተደርጎ ተስሏል፡፡

እነዚህ እውነታዎች ከአባይ ስም ጋር መጥፎና መልካም ስሜቶች እንደተቆራኙ ያመለክታሉ፡፡ በሐገራችን ውስጥ አባይ፣ ከወንዝ ስምነት በተጨማሪ የሰዎችና የድርጅቶች ስም ሆኖም ያገለግላል፡፡ በሐገር ደረጃ የታወቁት እነ ናይል ኢንሹራንስ፣ አባይ ባንክ፣ ግዮን ጋዝ ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንዲሁም አባይ፣ አባይነህ፣ አባይነሽ የሚባሉ የግለሰብ ስሞች በስፋት ይታወቃሉ፡፡ የነዚህ በአባይ ላይ የተመሠረቱ የድርጅትና የግለሰብ ስሞች በሀገር ደረጃ ለወንዙ ያለንን መልካም ስሜት የሚገልጹ ናቸው፡፡ ከሀገር ደረጃ ወረድ ብለን የወንዙ አጎራባች በሆኑ ከተሞች የምናየው የአባይን ስሞች ለሌሎች ድርጅቶች የመጠቀም ዝንባሌ ግን ከቦታ ቦታ የተለያየ ነው፡፡ ለዚህ እንደጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በደጀን እና በባህርዳር ከተሞች የሚገኙ በአባይ የተሰየሙ የድርጅቶች ብዛት ነው፡፡ በባህርዳር ዳር ከትንንሽ እስከትልልቅ ድርጅቶች በአባይ የተሰየሙትን ያህል፣ በደጀን ቁጥራቸው ጥቂት ነው፡፡ ይህ እውነታ ወንዙ በሁለቱ አካባቢዎች ነዋሪዎች ዘንድ ያሳደረውን ስሜት ያሳያል፡፡ በባህር ዳር አባይ የፈውስ፣ የበረከትና መዝናኛ/ውበት መገኛ ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ኗሪው ለአባይ ስም መልካም ስሜት አለው፡፡ ስሙም በብዛት ለሰዎችና ለድርጅቶች መጠሪያነት ያገለግላል፡፡ በደጀን አካባቢ ግን አባይ የሽፍታና የአራዊት መደበቂያ፣ በእግር ለመድረስና ለመመለስ ፈተናው የበዛ፣ እንደፈለጉት በቀላሉ የማይሻገሩት፣ በአጠቃላይ ከሚያበረከተው ጠቀሜታ ይልቅ የሚያደርሰው ተጽእኖ የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም ስሙ የመልካም ስሜት መገለጫ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ስሙን አዘውትሮ የድርጅትና የግለሰብ ስም የመማድረግ አዝማሚያ የለም፡፡

### 4. መደምደሚያ

በዚህ ጥናት የአባይን ስሞች የትመጣና ፍች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ የስመ-ተጸውኦ ፍች ጥናትን መሠረት በማድረግ የአባይ ስሞች የትመጣና ፍች ምን እንደሚመስል ለማሳየት ተመርምሯል፡፡ እስከዛሬ ስለአባይ ስሞች ይሰጡ የነበሩ ሀተታዎች የስሞቹን ምንጭ አንዴ ግብጻዊ፣ አንዴ አውሮፓዊ ሲያደርጉት ኖረዋል፡፡ ሆኖም ሀተታዎች ከወንዙ ጋር አብረው የኖሩ ህዝቦችን ታሪክ መሠረት በማድረግ ሲፈተሹ ውሃ የማያነሱ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ ይልቁንም የአባይን ስሞች ፍችና የትመጣ፣ ከወንዙ ጋር ከጥንት ጀምሮ ከኖሩ ህዝቦች ታሪክ አንጻር፣ ከህዝቦች የስም አወጣጥና ለውጥ ሥርዓት አንጻር በመመርመር የወንዙ ስሞች የትመጣም ሆነ ፍች ከጥንታውን ኢትዮጵያውን ጋር የተቆቆኘ መሆኑ ተገልጧል፡፡ በመጨረሻም በአሁኑ ጊዜ ከአባይ ስሞች ጋር ተያይዘው የሚገኙ ስሜቶች ምን ምን እንደሆኑ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም ከአባይ ስሞች ጋር አዎንታዊም አሉታዊም ስሜቶች እንደሚንጸባረቁ ተመልክቷል፡፡ ይህም በተለያዩ ጥናቶች እንደተገለጸው በስነቃል፣ በጥበብ ውጤቶች፣ እንዲሁም የአባይን ስሞች ለድርጅትና ለሰዎች መጠሪያነት በመገልገል እንደሚንጸባረቅ ተታይቷል፡፡ ወቅቱ ኢትዮጵያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለማጠናቀቅ የተቃረበችበትና ከግብጽ ጋር የሚደረገው ድርድርም የተጧጧፈበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህ ጽሑፍ ትንሽም ቢሆን አበርክቶ ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

## ዋቢዎች


የኢትየጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1962 ፡፡ *የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትየጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1980፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*፡ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡

አማን በላይ፡፡ 2009፡፡ *የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ* (2ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ኔባዳን ፐብሊኬሽን፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ 1962 ፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ግርማ አውግቸው፡፡ 2018 ፡፡ *ቋንቋና ነገድ በኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ማንነትና ቅደመታሪክ* (ቅጽ 1)፡፡ አዲስ አበባ፣ ዘ ሬድ ሲ ፕሬስ፡፡

ኪዳነወለልድ ክፍሌ፡፡ 1948 ፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት.

ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ፡፡ 2000 ፡፡ *የዓባይ ውሃ ሙግት*፡፡. አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡.

አስረስ የኔሰው፡፡ 1951 ፡፡ *ትቤ አክሡም መኑ አንተ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ፀጋዬ ገብረመድኅን፡፡ 1990 ፡፡ «ጉራቻ አካዋቃ» *ጦቢያ መጽሔት* 5(11)፡፡

Azevedo, J. 2013. *Simplified Coptic Dictionary* (Sadik Dialect) (2nd ed.). Lima, Peru: Peruvian Union University.

Bonnet, C. 2019. *The Black Kingdom of the Nile*. Cambridge, Massachusetts, London: Harvard University Press.

Butler, T. C. (Ed.). 1991. Entry for 'Gihon'. Holman Bible Dictionary. https://www.studylight.org/dictionaries/hbd/g/gihon.html.1991. Broadman and Holman. Retrieved 7/ 22/ 2020

Černý, J. 1976. *Coptic Etymological Dictionary*. Cambridge, London, New York, Melbourne: Cambridge University Press.

Damtew, I. 2016. Friend, Stranger, Enemy: Ethiopian Oral Traditions on the Abay (Blue Nile) River. *Ethiopian Renaissance: Journal of Social Sciences and Humanities*, 3(2), 21-38.

Degefu, G. T. 2003. *The Nile: historical, legal and developmental perspectives*. Victoria: Trafford Publishing.

Encyclopaedia, B. 2016. Nile River. *Encyclopedia Britannica* INC. Retrieved December 2, 2016

Erlich, H., & Gershoni, I. (eds.). 2000. *The Nile: Histories, Cultures and Myths*. Boulder, London: Lynne Riener Publishers.

Gebre, T. 2011. Nature, Religion and History: De/Mythologizing of the Romance of Ethiopia in 'Abbay' and Adefris. In J.K.S. Makokha, Egara Kabaji, Dominica Dipio, (Eds.). *East African Literature: Essays in Written and Oral Traditions,* (PP 46-57). (Berlin: Logos Verlag.

Hillel, D. 2005. *The Natural History of the Bible: an Environmental Exploration of the Hebrew Scriptures*. New York: Columbia University Press.

Hough, C. (Ed.). 2016. *The Oxford Handbook of Names and Naming*. Oxford: Oxford University Press.

Houston, D. 1926. *Wonderful Ethiopian of the Ancient Cushite Empire*. Oklahoma City: Universal Publishing Company.

Leslau, W. 1991. Comparative Dictionary of Geez (Classical Ethiopic). Wiesbaden: Otto Harrassowitz.

Nyström, S. 2016. Names and Meaning. In C. Hough, *Oxford Handbook of Names and Naming* (pp. 40-52). Oxford: Oxford University Press.

Oestigaard, T., & Gedef, A. 2011. Gish Abay: The Source of Blue Nile. In WIT *Transactions on Ecology and the Environment*, (pp 27-38).

Rizk, Y. L. (1999-2000, Dec- Jan 29-5). Egypt is Synonymous with the Nile. In *Al Ahram weekly* (20th Century Special Issue).

Saakana, A. S. 1991. *African Origin of Major World Religions* (2nd Ed.). London: Karnak House.

Tefla, B. 2000. The Father of Rivers: The Nile in Ethiopian Literature. In Erlich, H., & Gershoni, I. (eds.) (2000). *The Nile: Histories, Cultures and Myths*, (pp 153 -170). Boulder, London: Lynne Riener Publishers.

Tsegaye Gebre-medhin. 1991. African Origins of Trinity in Art and Religion: Ethiopian Roots in Egypto-Greek and Hebrew. In Saakana, A. S. (ed.) (1991). *African Origin of Major World Religions* (2nd ed.), (pp 99 -121). London: Karnak House (HOUSTON, 1926)

Van Langendonck, W., & Van de Velde, M. 2016. Names and Grammar. In C. Hough. *The Oxford Handbook of Names and Naming* (pp. 18-39). Oxford: Oxford University Press.

Williams, C. (1974). *The Destruction of Black Civilization: Great Issues of Race from 4500 B.C. to 2000 A .D.* Chicago: Third World Press.

Zabeeh, F. (1968). *What is in a Name? An Enquiry into the Semantics and Pragmatics of Proper Names.* The Hague: Martinus Nijh of.